የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 35
ADDIS ABABA 15th May, 2009

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፰/፪ሺ፩ ዓ.ም

የባህር ወለድ እፅዋትን ከመርከብ ቅብ ንጥረ ነገሮች ለመከላከል የተደረገ አለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፯፻፳፮

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 628/2009**

The Control of Harmful Anti Fouling Systems Convention Ratification Proclamation Page 4726

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፰/፪ሺ፩

## <u>የባህር ወለድ እፅዋትን ከመርከብ ቅብ ንጥረ ነገሮች ለመከላከል የተደረገ አለም አቀፍ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ</u>

የባህር ወለድ እፅዋትን የመርከብ ቅብ ንጥረ ነገሮች ለመከላከል የተደረገ የአለም አቀፉ የባህር ድርጅት ስምምነት እ.ኤ.አ. በ፪ሺ፩ የወጣ ስለሆነ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የባህር ወለድ እፅዋትን ከመርከብ ቅብ ንጥረ ነገሮች ለመከላከል የተደረገ አለም አቀፍ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፰/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 628/2009.

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE INTERNATIONL CONVENTION ON THE CONTROL OF HARMFUL ANTI-FOULING SYSTEMS</u>

**WHEREAS,** an International Convention in the control of harmful Anti-fouling systems has been adopted by the International Maritime Organization in 2001;

**WHEREAS**, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30th day of April, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "The Control of Harmful Anti Fouling Systems Convention Ratification Proclamation No. 628 /2009".

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

የባህር ወለድ እፅዋትን ከመርከብ ቅብ ንጥረ ነገሮች ለመከላከል እ.ኤ.አ. በ፪ሺ፩ የተደረገው የአለም አቀፍ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Convention

The Convention on the Control of Harmful Anti-fouling systems adopted in 2001, is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Ministry of Transport and Communications

The Ministry of Transport and Communications is hereby authorized to undertake in cooperation with the concerned governmental organs all acts necessary for the implementation of the convention.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**